የወርቅና የብር ባለቤት ሆኖ ሐቃቸውን የማይወጣ ሰው የትንሳኤ ቀን ለርሱ የእሳት ዝርግ ተዘርግቶለት በርሷ በጀሃነም እሳት ውስጥ ሳይቃጠል የሚቀር የለም። ጎኑም፣ ግንባሩና ጀርባውም የሚተኮስ መሆኑ አይቀርም።

ከአቡ ሁረይራ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው እንዲህ አሉ: «የአላህ መልክተኛ
(ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና እንዲህ ብለዋል: "የወርቅና የብር ባለቤት ሆኖ ሐቃቸውን የማይወጣ ሰው የትንሳኤ ቀን ለርሱ የእሳት ዝርግ ተዘርግቶለት በርሷ በጀሃነም እሳት ውስጥ ሳይቃጠል የሚቀር የለም። ጎኑም፣ ግንባሩና ጀርባውም የሚተኮስ መሆኑ አይቀርም።" በቀዘቀዘች ቁጥር እየተመላለሰች መጠኑ ሀምሳ ሺህ አመት የሚያህል ለሆነ ቀን ይተኮሳል። ይህም በባሮች መካከል ፍርድ ተፈርዶ መንገዱ ወደ ጀነት ወይስ ወደ እሳት ነው የሚለውን እስኪመለከት ድረስ የሚዘልቅ ነው።" "የአላህ መልክተኛ ሆይ! ግመልስ?" ተባሉ። እርሳቸውም "የትንሳኤ ቀን በሆነ ጊዜ የተስተካከለ ሰፊ መሬት ላይ ባለቤቱ ተጥሎ ግመሏ ዱንያ ውስጥ ከነበረችበት የበዛች ሆናና ከነበሩት አንድም ግልገል ሳትቀነስ በሸኾናዋ የምትረግጠውና በአፏ የምትነክሰው ቢሆን እንጂ ሐቋን የማይወጣ የግመል ባለቤት የለም። ከሐቋ መካከልም ለመጠጥ በምትወርድበት ቀን አልቦ (ለሚስኪን ማጠጣት) ነው። የመጀመሪያዋ ባለፈችበት ቁጥር ሌላኛዋ እየተመላለሰች መጠኑ ሀምሳ ሺህ አመት የሚያህል ለሆነ ቀን ታሰቃየዋለች። ይህም በባሮች መካከል ፍርድ ተፈርዶ መንገዱ ወደ ጀነት ወይስ ወደ እሳት ነው የሚለውን እስኪመለከት ድረስ ነው።" አሉ። ለርሳቸውም "የአላህ መልክተኛ ሆይ! ከብትና ፍየልስ?" ተባሉ። እርሳቸውም "የትንሳኤ ቀን በሆነ ጊዜ የተስተካከለ ሰፊ መሬት ላይ ባለቤቱ በአፍጢሙ ተጥሎ ከነርሱም መካከል አንድም ሳይጎድልና አንድም ቀንዱ የተጠመዘዘ፣ ቀንድ የሌለው ወይም ቀንደ ሰባራ ሳይኖር እያንዳንዷ በቀንዷ የምትወጋው በጥፍሯም የምትረግጠው ቢሆን እንጂ ሐቋን የማይወጣ የከብትና ፍየል ባለቤትም የለም። የመጀመሪያዋ ባለፈችበት ቁጥር ሌላኛዋ እየተመለሰች መጠኑ ሀምሳ ሺህ አመት የሚያህል ለሆነ ቀንም ታሰቃየዋለች። ይህም በባሮች መካከል ፍርድ ተፈርዶ መንገዱ ወደ ጀነት ወይስ ወደ እሳት ነው የሚለውን እስኪመለከት ድረስ የሚቀጥል ነው።" አሉ። ለርሳቸውም "የአላህ መልክተኛ ሆይ! ፈረስስ?" ተባሉ። እርሳቸውም "ፈረስ ሶስት አይነት ነው። ለሰውዬው ወንጀል የሆነች፣ ሰውዬውን የምትሸሽገው የሆነችና ለሰውዬው ምንዳ የምታስገኝ የሆነች አለች። ለርሱ ወንጀል የሆነችበትማ ለይዩልኝ፣ ለፉከራና በሙስሊሞች ላይ ሊዘመትባት የታሰበችው ናት። እርሷ ለርሱ የምትሸሽግ የሆነችውም በአላህ መንገድ አስሯት ከዚያም በጀርባዋና በጫንቃዋ ላይ ያለውን የአላህን ሐቅ ያልረሳ ነው። ይህቺም እርሱን የምትሸሽግ ናት። እርሷ ለርሱ ምንዳ የምታስገኝ የሆነችው ደግሞ በአላህ መንገድ ለሙስሊሞች ሊዘምትባት በቡቃያ ስፍራ ወይም በጨፌ ውስጥ ያሰራት ነው። በዚህ ቡቃያ ስፍራ ውስጥ ወይም በጨፌ ውስጥ አንዳችም በበላች ቁጥር ምንዳ ለርሱ ቢፃፍለት፣ የእበቷና
የሽንቷ ቁጥር ያህልም ለርሱ ቢፃፍለት እንጂ፤ የታሰረችበትን ገመድ አትቆርጥምም፣ ኮረብታን ወይም ኮረብታዎችን አትሮጥም አላህ በኮቴዋና በእበቷ ቁጥር ምንዳን ቢፅፍለት እንጂ፤ ባለቤቷ እርሷን ይዞ በወንዝ በኩል አያልፍምም እርሱ ሊያጠጣት ባይፈልግ እንኳ
ከወንዙ አትጠጣምም አላህ ለርሱ በጠጣችው ቁጥር ምንዳ ቢፅፍለት እንጂ።" አሉ። [ሶሒሕ ነው።] [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

ነቢዩ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና የተለያዩ የገንዘብ አይነቶችንና የትንሳኤ ቀን ዘካቸውን ያላወጣ ሰው ምንዳ ምን እንደሆነ ገለፁ። የመጀመሪያው: ወርቅ፣ ብርና በነርሱ ደረጃ ያለ ገንዘብና መገበያያ ሸቀጥ ነው። ይኸውም ዘካ ግዴታ ሆኖበት ያልወጣለትን ወርቅና ብር ነው። የትንሳኤ ቀን ሲሆን በዝርግ መልኩ የሚቃጠልም የሚቀልጥም ይደረጋል። በጀሃነም እሳት ውስጥም ትቀጣጠላለች በርሷም ባለቤቱ ይቀጣበታል። በርሷም ጎኑም፣ ግንባሩና ጀርባውም ይተኮሳል። በቀዘቀዘች ቁጥር ግለቷ ይመለሳል። አላህ በፍጡራን መካከል ፈርዶ ከጀነት ነዋሪዎች ወይም ከእሳት ነዋሪዎች መካከል ከአንዱ እስኪሆን የአንዱ ቀን መጠን ሀምሳ ሺህ አመት የሚያህል በሆነበት የእለተ ትንሳኤ ሙሉ ጊዜው በዚህ ሁኔታ ቅጣቱ ይቀጥላል። ሁለተኛው: ግዴታ የሆነው ዘካዋንና ሐቋን ያልተወጣላት የግመል ባለቤት ነው። ከግመል ሐቅም እርሷ ዘንድ ለሚገኙ ድሆች በማለብ ማጠጣት ነው። ይህቺ ግመልም ተልቃ፣ ሰብታና ከነበሩበት ቁጥር በዝተው ይመጣሉ። የትንሳኤ ቀን የተስተካከለ ሰፊ መሬት ላይ ባለቤቱ ይዘረጋል፣ ይጣላል፣ ለርሷ ይለጠጣል። በእግሮቻቸውም ይረገጣል፣ በጥርሶቻቸውም ይነከሳል። የመጨረሻዋ ግመል ባለፈች ቁጥር የመጀመሪያው ይመለሳል። አላህ በፍጡራን መካከል ፈርዶ ከጀነት ነዋሪዎች ወይም ከእሳት ነዋሪዎች መካከል ከአንዱ እስኪሆን ድረስም የአንዱ ቀን መጠን ሀምሳ ሺህ አመት የሚያህል በሆነበት በእለተ ትንሳኤ ሙሉ ጊዜውን በዚህ ሁኔታ ቅጣቱ ይቀጥላል። ሶስተኛው: ግዴታ የሆነበትን ዘካ የማያወጣለት የከብት፣ የፍየልና የበግ ባለቤት የሆነ ሰው ነው። ከነበሩበት መጠን ምንም

ሳይቀነስ በዝተው ይመጣሉ። የትንሳኤ ቀን የተስተካከለ ሰፊ መሬት ላይ ባለቤቱ ተዘርግቶ ይጣላል፣ ለርሷ ይለጠጣል። ከነርሱም መካከል ቀንዱ የተጠመዘዘ፣ ቀንድ የሌለውና ቀንዱ የተሰበረ አይኖርም። ይልቁንም የተሟላ ባህሪ ተላብሰው ነው የሚመጡት። በቀንዶቻቸውም ይወጉታል፣ በእግራቸውም ይረግጡታል። የመጨረሻዋ ባለፈች ቁጥር የመጀመሪያዋ ትመለሳለች። አላህ በፍጡራን መካከል ፈርዶ ከጀነት ነዋሪዎች ወይም ከእሳት ነዋሪዎች መካከል ከአንዱ እስኪሆን ድረስ የአንዱ ቀን መጠን ሀምሳ ሺህ አመት የሚያህል በሆነበት በእለተ ትንሳኤ ሙሉ ጊዜውን በዚህ ሁኔታ ቅጣቱ ይቀጥላል። አራተኛው: ፈረስ የሚያደልብ ነው። ይህም ሶስት አይነት ናቸው። አንደኛ: እርሷ ለርሱ ወንጀል የሆነችበት ናት። ይህም ለይዩልኝ፣ ለፉከራና ሙስሊሞችን ለመዋጋት የያዛት እንደሆነ ነው። ሁለተኛ: እርሷ ለርሱ የምትሸሽገው የሆነች ናት። ይህም በአላህ መንገድ ለመዋጋት የያዛት እንደሆነ ነው። ከዚያም ለፈረሷ በመቀለብ፣ ጣጣዋን በመቻል ከዚህም ውስጥ ኮርማዋን በማዘጋጀት ለርሷ መልካም የዋለ እንደሆነ ነው። ሶስተኛ: እርሷ ለርሱ ምንዳ የምታስገኝ የሆነች ናት። ይህም በአላህ መንገድ ለሙስሊሞች ለመዋጋት የያዛትና በቡቃያ ስፍራና በጨፌ ውስጥ ያሰማራት እንደሆነ ነው። ይህቺ ፈረስ አንድም አትበላም ለርሱ በበላችው ቁጥር ምንዳ ቢፃፍለት እንጂ፤ በእበቷና ሽንቷ ቁጥር ልክ ምንዳ ቢፃፍለት እንጂ፤ የምትታሰርበትን ገመድ ቆርጣ በምድር ከፍታ ላይ አትሮጥም አላህ ለርሱ በኮቴዋና እበቷ ቁጥር ልክ ምንዳን ቢፅፍለት እንጂ፤ ባለቤቱ እርሷን ይዞ በወንዝ በኩል ሲያልፍ እርሷን ማጠጣት ሳይፈልግም አትጠጣም አላህ በጠጣችው ቁጥር ለርሱ ምንዳ የሚፅፍለት ቢሆን እንጂ። ቀጥሎ ነቢዩ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና ስለአህያ እርሷም እንደ ፈረስ አምሳያ ናትን? ተብለው ተጠየቁ። እርሳቸውም: ከዚህች አጭር ከሆነችው አንቀፅ በቀር እርሷን የሚመለከት አንቀፅ አልወረደም። ይህቺ አንቀፅም ሁሉንም የአምልኮና የወንጀል አይነቶችን የምታጠቃልል ናት። ይህቺም አንቀፅ {የብናኝ ክብደት ያክልም መልካም የሰራ ሰው ያገኘዋል። የብናኝ ክብደት ያክልም ክፉን የሰራ ሰው ያገኘዋል።} [አዝዘልዘላህ:8] የምትለዋ የአላህ ንግግር ናት። አህያን ሲያደልብ አላህን ለመታዘዝ አልሞ ከሆነ የዚህን ምንዳ ያገኛል። ወንጀል ከሰራ ደግሞ የዚህን ቅጣት ያገኛል። ይህ አንቀፅ ሁሉንም ስራዎች የሚጠቀልል ነው።

http://sunnah.global/hadeeth/am/show/6611